# ፋኖ ተሰማራ

## ሀብታሙ አሰፋ (ከአሥመራ መንገድ)

ፋኖ ተሰማራ
ወገንህን አኩራ
እያለ ሲያቅራራ …"
የሚንቀለቀል ችቦ
በሕዝብ ትገል ተቀጣጥሎ
ብርሃኑ ሲፈካ
ጭቁኑ ሲያወካ
በደም የቀለመ
ፅኑ ሕዝባዊ ትግል
ውስጤ ግሞ ፋመ
ይታየኛል ያኔ
ረሀብተኛ ወገኔ
ሰርቶ በወዙ ሲከበር
ጠግቦ በልቶ ሲያድር
ደግሞም ይታየኛል
በመሣሪያ የፈነጩ
በጎሳ ያጋጩ
እድገት ያቀጨጩ
ጥርሳቸውን ሲያፏጩ
በማይናጋው አንድነቱ
ወገኔን ማኩራቱ
ፍትሕ በነፃነት
ሕዝባዊ ዳኝነት
ያለ አድሎ ፍራቻ
ያለ ቂም ጥላቻ
ሲከበር በአግባቡ
ጭቁኖች ሲያብቡ
ሁሉም ይታየኛል
በክፉ በሽታ በነገድ በጎሳ
        አትቀርም ይቀሯል
        ኢትዮጵያ አልቅሳ
እንዲመጣ ድሉ
        ወገኔ ተነሳ።